206

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

የ1999 ዓ.ም የስድስት ወራት ሰቅድ አፈጻጸም
ግምገማ ሪፖርት

ጥር 1999
አዲስ አበባ

27

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

የ1999 ዓ.ም የስድስት ወራት ሰቅድ አፈጻጸም
ግምገማ ሪፖርት

ጥር 1999
አዲስ አበባ

ማውጫ

	አርዕስት	ገጽ
1	መግቢያ	1
2	የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ	3
	2.1 የተፈጥሮ ሃብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት	3
	2.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት	5
	2.3 የኢንዱስትሪ፣ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት	7
3	የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት	8
	3.1 3ኛው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራን በተመለከተ	8
	3.2 የቆጠራ ካርታ ሥራ እንቅስቃሴ	11
	3.3 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት	11
	3.4 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት	14
4	የ1999 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም	15
5	የሜቶዶሎጂን ሥራ በተመለከተ	15
6	የመረጃ ማቀነባበርን ሥራ በተመለከተ	17
7	የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን የማሻሻል ሥራን በተመለከተ	19
8	የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ሥራን በተመለከተ	20
9	የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት ሥራን በተመለከተ	23
10	የኦዲት ሥራን በተመለከተ	25
11	የሕግ ሥራን በተመለከተ	26
12	የፕላንና ፕሮግራም ሥራን በተመለከተ	27
13	የሰው ሃብት ሥራ አመራር ሥራን በተመለከተ	27
14	የፋይናንስ ሥራን በተመለከተ	28
15	የቴክኒክና ንብረት አስተዳደር ሥራን በተመለከተ	33
16	የሕትመት ሥራን በተመለከተ	35
17	ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች	35
18	ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎች	36

የ1999 ዓ.ም የስድስት ወራት
ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት

1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሥነ-ሕዝብ ሁኔታዎችን የሚመለክቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በበጀት ዓመቱ ለመተግበር በዕቅድ ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። እነዚህ መረጃዎች እንደተጠቃሚው ፍላጐት ለዕቅድ ዝግጅት፣ ለምርምርና ለልማት ክንውኖች ግምገማ የሚጠቅሙ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ በሁለት የተለያዩ ፕሮጀክቶች (የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮጀክትና የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት) ስር በርካታ ጥናቶችን ለማከናወንና በ1998 የመረጃ መሰብሰብ ተግባራቸው ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀላቸውንና በከፊል የመረጃ ቅንብር ሥራቸው የተጀመሩላቸውን ጥናቶች ለማጠናቀቅ እየሠራ ይገኛል።

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በአዲስ ዕቅድ እየተከናወኑ ያሉ፣

1.1 በተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮጀክት

1.1.1 የግብርናና የተፈጥሮ ሃብትና ስታቲስቲክስ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣
- የሰብል ምርት ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት፣
  - የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት
  - የሰብል ምርት ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት
  - የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት
- የሰፋሬ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት፣
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ኃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት፣

1.1.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣
- የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች ዝግጅት ናቸው።
- ዓለም አቀፍ የዋጋ ንፅፅር ጥናት በአፍሪቃ (ቀጣይ ጥናት)፣

1.1.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድና ትራንስፖርት ስታቲስቲክስ

- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
- ወቅታዊ የማማረቻ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት፣

- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የምርት መጠንና የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- የወጪ ንግድ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር፣

1.1.4 ሌሎች ተጨማሪ ጥናቶች

- ከግብርና ወጪ በገጠር የሥራ መስክ ጥናት
- የምግብ ዋስትና ጥናት የመረጃ ቅንብር ሥራ

1.2 በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት

1.2.1 የቆጠራ ቦታ ካርታ ዝግጅት ሥራን ማጠናቀቅ፣

1.2.2 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ማካሄድ

- የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የስካኒንግ መስራ ቆጠራ ማካሄድ
- ለዋናው ቆጠራ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶችን በማጠናቀቅ ቆጠራውን ማከናወን፣

1.3 ከ1998 ዓ.ም ወደ 1999 ዓ.ም በዕቅድ የተሸጋገሩ ጥናቶች

1.3.1 በግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ስታቲስቲክስ

- የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት
- የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት
- የመሬት አጠቃቀም ጥናት
- የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት
- የሰፋፊና መካከለኛ የድርጅት እርሻዎች ጥናት

1.3.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

- የቤተሰብ ገቢ፣ፍጆታና ወጪ ጥናት መረጃ ቅንብር ሥራ፣

1.3.3 የሥነ-ሕዝብና ማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናቶች

- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የባሕሪ ቅኝት ጥናት
- የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት ናቸው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን ጥናቶች በበጀት ዓመቱ ለማከናወን መ/ቤቱ ከመንግሥት በተመደበ የካፒታል በጀት፣ ከተለያዩ የልማት አጋሮች በተገኘ ፋይናንስ፣ እና በመ/ቤቱ አማካይነት ጥናት እንዲሰራላቸው ከተጠየቁ መ/ቤቶች በተገኘ ገንዘብ ባለው ቋሚና የኮንትራት ሰራተኞች በመታገዝና መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ሥራዎቹን እያከናወነ ይገኛል፡፡ በዚህ ሪፖርት ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ (ከሐምሌ 1 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ

30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ) የተከናወኑ ሥራዎች፣ የፋይናንስ አጠቃቀምና በሥራ ሂደት የታዩና በበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለማካተት ተሞክሯል፡፡

2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ

2.1 የግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ስታቲስቲክስ

2.1.1 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት

የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ከነሐሴ ወር 1998 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ እስከ ጥቅምት 15 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ባሉት ቀናት ከመላው አገሪቱ በናሙና በተመረጡ የገጠር ቆጠራ ቦታዎች ላይ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የመረጃ መሰብሰቡ ሥራ ተጠናቋል፡፡ ለዚህ ጥናት ባለፉት ስድስት ወራት ይከናወናል ተብሎ በዕቅድ የተያዘው 93.25% ሲሆን፤ የተከናወነው 100% በመሆኑ በዕቅድ ከተያዘው በላይ በመከናወኑ የጥናቱ ውጤት ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

2.1.2 የግብርና ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት

በዚህ ጥናት ስር የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት፣ የመሬት አጠቃቀም ጥናት እና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት የሚጠቃለሉ ሲሆን፤ ባለፉት ስድስት ወራት ሊከናወን የታቀደው 50.45 % ፣59.07 % እና 59.07 % እንደቅደም ተከተላቸው ነው፡፡ በመሆኑም ባለፉት ስድስት ወራት መጨረሻ ላይ የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት ከዕቅዱ 44.5ቱ ወይም 88.2 ከመቶ፣ የመሬት አጠቃቀም ጥናት እና የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት እያንዳንዳቸው ከተያዘው ዕቅድ 53.2ቱ ወይም 90.1 ከመቶ ተከናውኗል፡፡

2.1.3 የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ላይ የቤት እንስሳት የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናትን ለማካሄድ በዕቅድ የተያዘው 74.66 በመቶ ሲሆን፤ በስድስት ወሩ መጨረሻ ላይ የተከናወነው 70.5 ቱ ነው፡፡ ይህም በዕቅድ ከተያዘው 94.43 በመቶው ነው፡፡

2.1.4 የሰፋሬ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት

በዕቅድ ዘመኑ ባለፉት ስድስት ወራት ለማከናወን በዕቅድ የተያዘው የሰፋሬ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት 58.25% ለማከናወን ሲሆን፤

እስካሁን ድረስ 48.25% ያህሉን ለማከናወን ተችሏል። ይህም ከዕቅዱ 82.83% እንደሆነ ያመለክታል።

2.1.5 <u>ከ1998 ወደ 1999 ዓ.ም የተሸጋገሩና ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች</u>

ሀ. <u>ከ1998 ወደ 1999 ዓ.ም የተሸጋገሩ ሥራዎች</u>

- በ1998 የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የመኸር ወቅት በሰብል የተያዘ መሬት ስፋትና ምርት መጠን፣ የ1998 ዓ.ም. መኸር ወቅት የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት፣ እንዲሁም የመሬት አጠቃቀም ጥናት ተጠናቀውና ሪፖርቶቹ ታትመው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል።

- በ1998 የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር የተጠናቀቀላቸው የበልግ ወቅት የመሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት እና የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት ተጠናቀው ሪፖርቶቹም ታትመው ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጩ ተደርጓል።

ለ. <u>ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች</u>

- ለ1999 ዓ.ም. ለሚከናወኑ የሰብል ምርት ትንበያ፣ ለዋናው መኸር ወቅት የናሙና ጥናት፣ የቤት እንስሳትን የሚመለከቱ መረጃዎች ሊያስገኙ የሚችሉ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል።

- በ1999 ዓ.ም. ለሚከናወነው ግብርና ጥናት በመስክ ሥራ ለሚሰማሩ ሠራተኞች በዋናው መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለአንድ ወር ሥልጠና ተሰጥቷል። እንደዚሁም ለሰብል ትንበያ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፌኬሽን መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

- መ/ቤቱ በ1999 ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ጠቃሚ የሚሆኑ የግብርናና የተፈጥሮ ሃብት መረጃዎችን በማጠናቀር ለሚመለከተው ክፍል እንዲደርስ ተደርጓል።

- በሰኔ እና በሐምሌ ወር 1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የበልግ ጥናት የመጠይቅና የመመሪያ ዝግጅት እየተከናወነ ይገኛል።

2.1.6 ከግብርና ወጪ በገጠር የሥራ መስክ ጥናት

ይህ ጥናት የሚካሄደው ከዓለም ባንክ በተገኘው 99,962 ዶላር የበጀት ድጋፍ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ ከጠቅላላ የጥናቱ ተግባራት ውስጥ የመጠይቅ ዝግጅትና ሕትመት እንዲሁም የመስክ ሠራተኞች ስልጠና ተከናውኖ፤ የመረጃ መሰብሰቡ ሥራ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቋል። እንዲሁም ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ኤዲቲንግና ኮዲንግ የማድረግ ተግባር እና ጥናቱ ከሚያካትታቸው አራት ክልሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የአማራ ክልል መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ለመጀመር ዝግጅቱ ተጠናቋል።

2.1.7 የምግብ ዋስትና ጥናት

መ/ቤቱ ከምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ ጋር በመተባበር የምግብ ዋስትና ጥናት ለማካሄድ በተደረገው ስምምነት መሠረት ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ተጠናቀውና በመስክ መረጃ ተሰብስቦ በማጠናቀቅ የመረጃ ቅንብር ሥራ በማከናወን የተጣራ መረጃ (cleaned database) ለምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ እንዲደርስ ተደርጓል።

2.1.8 የምግብ አቅርቦትና የሰብል ግምገማ

የመ/ቤቱ ባለሙያዎች ከFAO የምግብ አቅርቦትና የሰብል ግምገማ ቡድን ጋር በመሆን ለሦስት ሣምንታት የመስክ ግምገማ እንዲሳተፉ የተደረገ ሲሆን፤ የመስክ ግምገማው ውጤት ለ1999 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣ ማመሣከሪያነት መ/ቤቱ እንዲጠቀምበት ተደርጓል።

2.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

2.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክስ

ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት

የበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ የአምራቾች ዋጋ ጥናት የሐምሌ ወር 1998 እና የነሐሴ ወር 1998 ዓ.ም ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች የተሠራጨ ሲሆን፤ የመስከረም እና የጥቅምት 1999 ዓ.ም ጥናት መረጃ ተቀነባብሮ ለህትመት ተልኳል። የኅዳር ወር 1999 ዓ.ም መረጃ በመቀነባበር

ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ባለፉት ስድስት ወራት የታቀደው 39.29 በመቶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

ለ. <u>ወርሃዊ የዕቃዎችና የአገልግሎት ዋጋ ጥናት</u>

ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ወርሃዊ የዕቃዎችና አገልግሎት ዋጋ ጥናትን በተመለከተ ለመሥራት በዕቅድ ተይዞ የነበረው 39.68 % ሲሆን፤ የተከናወነው 39.68% ወይም የዕቅዱ 100 % ነው፡፡

ሐ. <u>ወርሃዊ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ</u>
<u>የአገር አቀፍና የክልሎች</u>

የአገር አቀፍና የክልሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ ከሐምሌ ወር 1998 እስከ ኅዳር ወር 1999 ዓ.ም ድረስ ያለው በየወሩ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ የታህሳስ ወር 1999 ዓ.ም አሃዝ እየተቀነባበረ ይገኛል፡፡

<u>የአዲስ አበባ ከተማ</u>

የአዲስ አበባ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ አሃዝ ከሐምሌ ወር 1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ ወር 1999 ዓ.ም ድረስ ያለው በየወሩ ተቀነባብሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች በወቅቱ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

መ. <u>ከ1998 ወደ 1999 ዓ.ም. የተሸጋገሩ ሥራዎች</u>

የሰኔ ወር 1998 ዓ.ም. የአገር አቀፍ፣ የክልሎችና የአዲስ አበባ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ በ1999 ዓ.ም. የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ተቀነባብሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

ሠ. <u>የዓለም አቀፍ ንዕዕር መረሃ - ግብር በአፍሪካ</u>

- ይህ ጥናት በአፍሪካ ልማት ባንክና በምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ የንግድ ቀጠና ጋር በመተባበር የሚካሄድ ነው፡፡በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት፣ መረጃ የመሰብሰቡ ሥራ ተጠናቆ፣ የዳታ ኢዲቲንግ፣ኮዲንግ፣ኢንትሪ እና ቬሪፌኬሽን ተግባርን በማጠናቀቅ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት መረጃ ወደአፍሪካ ልማት ባንክ ተልኳል፡፡

እንዲሁም የሁለተኛው ሩብ ዓመት መረጃ የዳታ ኤዲቲንግ፣ ኮዲንግ፣ ኢንትሪ እና ቬሪፊኬሽን ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

- የዚህ ጥናት አካል የሆነው የመድሃኒቶች ዋጋ መረጃ የመሰብሰብ ሥራ በየሩብ ዓመቱ ማለትም በነሐሴ ወር 1998 ዓ.ም እና በጎዳር ወር 1999 ዓ.ም ተከናውኗል፡፡

2.2.2 <u>የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት</u>

በ1997/98 በሁለት ዙር የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት መረጃ የመገምገም ሂደት በኤጀንሲው ተጠናቆ ጥሬ መረጃው ጥልቅ ትንተና እንዲካሄድበት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተልኳል፡፡

2.2.3 <u>ልዩ ልዩ ሥራዎች</u>

- የአምራቾች ዋጋ ጥናትና ለወርሃዊ የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ዋጋ ጥናት የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ በማዘጋጀትና ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ በማዘጋጀት ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- የገጠር መዋዕለ ነዋይ ፍሰት ሁኔታ ጥናት ለማካሄድ ከአለም ባንክ ጋር በተደረገ ስምምነት መሰረት የቤተሰብ በጀትና የኑሮ ሁኔታ ክትትል ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

- መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ መጽሔት የሚያገለግሉ መረጃዎች ከልዩ ልዩ መ/ቤቶችና ከቡድኑ ተሰባስበውና ተጠናቅረው ለሚመለከተው ክፍል ተልኳል፡፡

2.3 <u>የኢንዲስትሪ፣ ንግድ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ</u>

2.3.1 <u>የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናቶች</u>

- የወቅታዊ የማምረቻ የንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት ባለፉት ስድስት ወራት 25.75%ቱን ለማከናወን ታቅዶ የመረጃ ማሰባሰቡ፣ የማቀነባበሩና የሪፖርት ዝግጅቱ ሥራ ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡ በመሆኑም የተያዘው ዕቅድ ሙሉ በሙሉ መከናወኑን ያመለክታል፡፡

- የተፈበረኩ ዕቃዎችን ምርት መጠንና የአምራቾች ዋጋ ጥናትን በስድስት ወራት ውስጥ 44.5% ለማከናወን በታቀደው መሠረት ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

2.3.2 <u>ከ1998 ወደ 1999 የተሸጋገሩና ሌሎች ሥራዎች</u>

- ከApril 2006-June 2006 ድረስ ያለው የአምራቾች ዋጋ ኢንደክስ ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

- ለመ/ቤቱ ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት፣ ለትራንስፖርትና መገናኛና ስታቲስቲክስ መጽሔት የሚያገለግሉ መረጃዎች ከየመ/ቤቶች ተሰብስበውና የማቀነባበሩ ሥራ ተከናውኖ ለሚመለከተው ክፍል ተልኳል፡፡

- ለበርካታ ተጠቃሚዎች መረጃ የመስጠት ሥራ ተከናውኗል፡፡

3. <u>የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት</u>

3.1 <u>3ኛው ሕዝብና ቤቶች ቆጠራን በተመለከተ</u>

ለ3ኛ ጊዜ በመላው አገሪቱ በግንቦት ወር 1999 ዓ.ም ለሚካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ባለፉት ስድስት ወራት የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ሥራዎቹ በአብዛኛው ካለፉት ዓመታት ቀጣይነት ያላቸው ሲሆኑ፤ በጀት ዓመቱ ቆጠራው ተካሄዶ የሚጠናቀቅበት በመሆኑ ጐላ ብለው የሚታዩ ተግባራት ናቸው፡፡ ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

3.1.1 <u>የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የሎጂስቲክስ ዝግጅትን በተመለከተ</u>

የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ሥራን ለማከናወን የተለያዩ የሎጂስቲክስ ዝግጅቶች ማድረግ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም፡፡ በመሆኑም የቆጠራውን ሎጂስቲክስ ጠንካራ ለማድረግ ሥራው የተጀመረው ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን፤ በተለይም ባለፉት ስድስት ወራት በመንግሥት የተለያዩ ቁሣቁሶችን ለመግዛት የካፒታል በጀት የተመደበ ቢሆንም፤ ኤጀንሲው ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ተከታታይ ውይይት ለቆጠራው መረጃ ማቀነባበሪያ የሚውሉ 11 ስካነሮች፣ የጽ/መሣሪያዎች፣ ኮምፒውተሮች፣ የቆጣሪ ቦርሣዎች ወዘተ. ወጪን በተባበሩት መንግሥታት የሥነ-ሕዝብ ፈንድ፣ በኔዘርላንድ እና በአየር ላንድ መንግሥታት ድጋፍ እንዲሸፈኑ

ተደርጓል፡፡ አጠቃላይ ለቆጠራው የሚውሉ አስፈላጊ የሆኑ ቁሣቁሶች ግዥም ከ95 በመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ቀሪው እስከ ጥር 30/1999 ዓ.ም ድረስ ይከናወናል፡፡

3.1.2 የፋይናንስ አፈፃፀም መመሪያ ዝግጅት

የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ኃይልና ቁሣቁስ የሚጠይቅ ግዙፍ ሥራ በመሆኑ ሥራውን ለማስፈፀም የሚውለው/ የሚወጣው ገንዘብም እንዲሁ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ ለቆጠራው የተፈቀደውን በጀት በአግባቡ ለታቀደለት ሥራ በትክክል መዋሉን እና ወጪዎችና ማስረጃዎች በትክክል መያዛቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ እንዲሁም በየደረጃው የተቋቋሙት የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽኖችና የፋይናንስ ተቋማት በጀቱን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር መከተል የሚገባቸውን የሥራ ድርሻ አካቶ የያዘ የፋይናንስ አፈፃፀም መምሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል ከተካሄዱት ተመሣሣይ ቆጠራዎች የተገኙ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን እንዲሁም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ዘርፎች በተገኘ ሙያዊ እገዛ ለቆጠራው የፋይናንስ መመሪያ ተዘጋጅቶ በየክልሉ እየተሠራጨ ይገኛል፡፡

3.1.3 ስለቆጠራው የትምህርትና ቅስቀሣ ተግባርን በተመለከተ

የቆጠራውን አጠቃላይ ሥራዎች /የዝግጅትና የተግባር ምዕራፎች/ በተገቢው ፍጥነትና ጥራት እንዲሁም በተፈቀደው በጀት ያለምንም ችግር ለማከናወን በቆጠራው ተግባር ላይ የሚሰማሩ ሁሉም አካላት ከሚሰጡት ድጋፍ በተጨማሪ ስለቆጠራው ዓላማ፣ ጥቅሞች፣ የሥራው አፈፃፀም ወዘተ... ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የተለያዩ የትምህርትና ቅስቀሣ ሥራዎች በየደረጃው ለሚገኙ የሥራ ኃላፊዎችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ተሰጥቷል፡፡ ለዚህም እንዲረዳና በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ለሚካሄደው የግንዛቤ ሥራ አንድ ወጥ ለማድረግ የሚያስችል የትምህርትና ቅስቀሣ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ቁጥራቸው 500 ለሚደርሱ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለሚገኙ የቀበሌ አመራር አካላትና ሕዝባዊ ድርጅቶች የግማሽ ቀን ሴሚናር ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በክልሎች ማለትም በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያና በጋምቤላ የሥነ-ሕዝብና ስታቲስቲክስ ቢሮዎች በተዘጋጁ ሴሚናሮች ላይ በመገኘት ስለቆጠራው ዓላማ፣ ጥቅምና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ገለፃዎች ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ መምሪያ ለጋዜጠኞች በተሰጠ ሴሚናር ላይ ቆጠራውን አስመልክቶ የአንድ ቀን ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በመስከረም ወር 1999 ዓ.ም.

ላይ በተደረገ የፕላዝማ የትምህርት ጉባኤ ላይ ለተሳተፉ መምህራን ስለቆጠራው አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሰፊ ማብራሪያና ገለፃ ተደርጓል፡፡

3.1.4 ለቆጠራው የገንዘብና ሌሎች ድጋፎችን ማፈላለግን በተመለከተ

የቆጠራው ውጤት ዋነኛ ተጠቃሚ መንግሥትና ሕብረተሰቡ ቢሆንም መንግስታዊ ያልሆኑና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም የቆጠራውን ውጤት ይጠቀሙበታል፡፡ በመሆኑም የቆጠራውን በጀት በከፍተኛ መጠን እየደገፈ ያለው መንግሥት ሲሆን፤ ተጠቃሚ የሆኑ ሌሎች አካላትም ድጋፍና ትብብር እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ ስለቆጠራው አጠቃላይ ስትራቴጂና የአፈፃፀም ዕቅድ /Strategy and Implementation Plan/ ተዘጋጅቶ ለለጋሽ ድርጅቶችና ሌሎች አካላት በማሰራጨት ለቆጠራው ማስፈፀሚያ ድጋፍና ትብብር ለማሰባሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ~~በዚሁም መሠረት~~ ከተባበሩት መንግሥታት የሥነ-ሕዝብ ፈንድ (UNFPA) 2,039,200 USD (የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ከተጀመረ ጀምሮ)፤ ከተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት (UNDP) 2,300,000 USD፤ከአየር ላንድ መንግሥት 144,000 USD ከኔዘርላንድ መንግሥት 42,000 USD ከተባባሩት መንግሥታት የሕፃናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) 200,000 USD በጠቅላላው 4,725,220 USD የተገኘ ሲሆን፤ በተጨማሪ ከእንግሊዝ መንግሥት የልማት ድርጅት (DFID) እንደ ኤ.አ ከ2007-2011 ለሚደረጉ የቆጠራ ተግባራት (በሶማሌ ክልል የሚካሄደውን ለሣተላይት ኢሜጀሪ ሥራ ጨምሮ) 7 ሚሊዮን ፖውንድ ~~ለመስጠት በእንቅስቃሴ ላይ እንደሆኑ ተረጋግጧል~~፡፡ ተገኝቷል፡፡

3.1.5 የቢሮና የመጋዘን ችግርን በተመለከተ

ኤጀንሲው ያለበትን የቢሮና የመጋዘን ችግር ለማቃለል ላለፉት ተከታታይ ዓመታት መፍትሄ በመንግሥት በኩል እንዲሰጠው ጥያቄ ማቅረቡ ይታወቃል፡፡ በተለይም ደግሞ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚካሄደው 3ኛው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ከግዙፍነቱ በተጨማሪ ለሥራው የሚደረገው አጠቃላይ ዝግጅት ሰፊ በመሆኑ ቆጠራው አስከሚጠናቀቅ ድረስ (ለሁለት ዓመት ተኩል ያክል) የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤትን እንዲጠቀምበት ተወስኖ ሥራው እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ኤጀንሲው አዲስ ቢሮ እንዲገነባ በመፍቀዱ ለግንባታው ሥራ የተለያዩ የዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

3.2 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ እንቅስቃሴ

3ኛውን የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ለማከናወን በቅድሚያ መሠራት ከነበረባቸው ተግባራት ውስጥ ዋነኛው የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ነው፡፡ በመሆኑም ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ 9753 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ የተካሄደ ሲሆን፤ እስከ ታህሣስ 30/1999 ዓ.ም ድረስ በአጠቃላይ 82,709 ቆጠራ ቦታ ካርታ ከጋምቤላ በስተቀር በሁሉም ክልሎች/ መስተዳድሮች ከሞላ ጐደል ተጠናቋል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ በትግራይ ኢብሮ ወረዳ ብቻ ሲቀር፣ አማራ ሙሉ በሙሉ፣ ኦሮሚያ አንድ የአርብቶ አደር ወረዳና ጥቂት ቀበሌዎች፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ሐረሪ፣ አዲስ አበባና ድሬደዋ መስተዳድሮች ሙሉ በሙሉ እንዲሁም ደቡብ ብ/ብ/ሕ በከፋ ዞን አራት የአርብቶ አደሩ ቀበሌዎች በስተቀር ሥራው ተጠኗቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአፋር ክልል እስከ ጥር 30/1999 ዓ.ም ድረስ ይጠናቀቃል ተብሎ በዕቅድ ተይዟል፡፡ የቆጠራው ካርታ ሥራው ተግባሩን የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ከያዘው በኋላ በልዩ ትኩረት፣ የተሻለ አሠራርና የአፈጻጸም ክትትል በመደረጉ ከዕቅድ በላይ ለመሥራት ተችሎአል፡፡ ይኸውም ሥራው በታህሣስ ወር በአብዛኛው ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደ ቢሆንም በዚህ ወቅት እንደሚሠራ ያልታቀደውን የአፋር ክልልን ጨምሮ ከዕቅድ በላይ ውጤታማ የሆነ ሥራ ለማከናወን ተችሎአል፡፡

3.3 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

3.3.1 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የሙከራ ጥናት

- ከነሐሴ 14 - 28/1998 ዓ.ም ድረስ በየክልሉ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለተመለመሉ መምህራን ሥልጠናውን በመስጠት የሙከራ ቆጠራው ተካሄዷል፡፡

- የሙከራ ቆጠራው ውጤት ከተለመደው አሠራር በተለየ መንገድ በስካኒንግ ቴክኖሎጂ በጥራትና በፍጥነት እንዲዘጋጅ በመታሰቡ የሚመለከተው አካል ወደ እንግሊዝ አገር በመሄድ የስካኒንግ መጠይቁን ከሚያዘጋጀው ድርጅት ጋር በመሆን መጠይቁ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ የተዘጋጀው መጠይቅም ወደዋናው መ/ቤት በኢንተርኔት ተልከው በሚመለከታቸው ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጐ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሣቦች ተካተው መጠይቁ ተዘጋጅቶ የሙከራ ቆጠራው ተካሂዷል፡፡

- የሙከራ ቆጠራው በሚካሄድበት ወቅት የሚመለከታቸው ባለሙያዎች በመስክ በመገኘት የታዩ ችግሮችንና ጠንካራ ጐኖች በመለየት ሪፖርት ቀርቧል፡፡ የሙከራ ጥናቱ የመረጃ ቅንብር ተካሄዶ ለዋናው ቆጠራ መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎችና ማሻሻያዎች ተለይተዋል፡፡

- የብሔራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ባሣለፈው ውሣኔ መሠረት የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽኖች በክልል ደረጃ እየተቋቋሙ ሲሆን፤ እስከ ታህሣስ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በአዲስ አበባ፣ በጋምቤላ፣ ድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል፣ በሐረሪ፣ በደቡብና በኦሮሚያና በአማራ ክልል እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡

- በዋናው ቆጠራ ለሚደረገው ስልጠና እንዲረዳ በሙከራ ቆጠራው ላይ የተሣተፉ መምህራን (ቆጣሪና ተቆጣጣሪዎች) ጋር ውይይት በማድረግ ለስልጠና ዝግጅቱ ጠቃሚ ማሻሻያዎች ተገኝተዋል፡፡

3.3.2 የቆጠራ መጠይቆች ሕትመት

የቆጠራው መጠይቆችና ቅጾች የሚታተሙት በእንግሊዝ አገር በዲ.አር.ኤስ ድርጅት አማካኝነት ሲሆን፤ የሕትመቱ ሥራ ከህዳር 24 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ መጠይቆቹ ታትመው ከተጠናቀቁ በኋላ በቅደም ተከተል በ3 ዙሮች ወደ አገር ወስጥ የሚገቡ ሲሆን፤ የመጨረሻው በመጋቢት ወር አጋማሽ ላይ እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡ መጠይቆች አገር ውስጥ ለማሣተም ያልተቻለው መጠይቆቹን ለስካኒንግ መሣሪያ በሚመች መንገድ ዲዛይን የሚያዘጋጅ ልምድ ያለው የሕትመት ድርጅት በአገር ውስጥ ባለመኖሩና ስካነሮቹ በተመረቱበት እንዲሁም የመጠይቆች ሕትመትና ዲዛይን የሚዘጋጅበት ተመሣሣይ ድርጅት ሲሆን በሥራ ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች አስቸኳይ መፍትሔ ለማግኘት ሲባል ነው፡፡

3.3.3 የቆጣሪዎችንና የተቆጣጣሪዎችን መመሪያ ማሻሻልና ማተም

በቆጠራው የሚሰበሰቡ መረጃዎች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው አንድ ወጥ በሆነ የአሠራር መመሪያ እንዲሰበሰቡ በሥራው ላይ ለሚሳተፉ ሠራተኞች መመሪያ ማዘጋጀት ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል ተዘጋጅተው የነበሩ የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያን በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉት የሙከራ ቆጠራዎች በተገኙና በተደረጉ ግምገማዎች የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት ሁለት

ጊዜ ማሻሻያ ተደርጐባቸውና ለስካኒንግ የተዘጋጁ መጠይቆችንና ቅጾችን ለመሙላት በሚያስችል መንገድ ተዘጋጅተው የሕትመት ሥራቸው ተጠናቋል፡፡

3.3.4 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አካላት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነትን ማዘጋጀት

3ኛውን የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በተሣካ ሁኔታ ጀምሮ ለመጨረስ እንዲቻል ከክልል አንስቶ እስከ ወረዳ መስተዳድር ደረጃ ለሚቋቋሙት የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽኖች እንዲሁም በገጠርና በከተማ ቀበሌዎች ደረጃ ለሚቋቋሙት የቆጠራ ኮሚሽኖች ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ተዘጋጅተዋል፡፡ የተዘጋጀው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ለመፈፀም በሚያስችልና በእያንዳንድ ኮሚሽን ስር ለሚደራጁ አካላት ማለትም ለትምህርትና ቅስቀሳ፣ የቆጠራ ጽ/ቤት ኃላፊ፣ ቆጠራ የመስክ የቴክኒክ አገልግሎት ኃላፊ፣ የአስተዳደርና ፋይናንስ እንዲሁም የኦዲት አገልግሎት ኃላፊዎች በሚመለከት ሲሆን፤ በየደረጃው በሚገኙ ባለሙያዎችና የአመራር አባላት ተገምግሞና የመጨረሻ መልክ እንዲይዝ ተደርጐ በበቂ ኮፒ ታትሞ በየክልሉ ለተቋቋሙ ኮሚሽኖች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

3.3.5 የቆጠራውን ውጤት ለማቅረብ የሚችል የታቡሌሽን ዕቅድ /Tabulation Plan/ ማዘጋጀት

በቆጠራው በርከት ያሉ የሥነ-ሕዝብ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም በአገሪቱ የሚገኙ ቤቶች ሁኔታን የሚያንፀባርቁ መረጃዎች ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡ በመሆኑም እነዚህ የተሰበሰቡ መረጃዎች በሦስት የተለያዩ ሪፖርቶች ማለትም የተለያዩ መረጃዎችን የያዙ ሠንጠረዦች በስታቲስቲካል ሪፖርት /Statistical Report/ እንዲሁም የትንተና ሠንጠረዦች ሪፖርት / Analytical Report / በተጨማሪም እነዚህን ሁለት ሪፖርቶች ጠቅለል በማድረግና ለውሣኔ ሊረዱ የሚችሉ ግልጽና ቀላል አቀራረብ ያላቸው ማጠቃለያ ሪፖርቶች /Summary Report/ ለማዘጋጀት ታቅዷል፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የሚረዱ 150 የተለያዩ የሠንጠረዥ ዓይነቶችን የያዘ ታቡሌሽን ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡

3.3.6 የቆጠራውን አጠቃላይ የሥራ ሂደት በሚመለከት

ለቆጠራው የሚደረገው ዝግጅት በአጠቃላይ በኮሚሽኑና በኮሚሽኑ ጽ/ቤት አመራር ልዩ ክትትልና የሥራ ሂደት ግምገማ እየተደረገበት በመከናወን ላይ ያለ ፕሮጀክት ነው፡፡ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት /የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ/ የአመራር አካላት በሳምንት ሁለት ጊዜ በመደበኛነትና ልዩ ስብሰባዎችንና በየሥራ ክፍሉ

በግንባር በመገኘት ያላሰለሰ ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ሥራው በአብዛኛው ከዕቅድ በላይ በተሳካ ሁኔታ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

3.4 <u>ማኅበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ</u>

- የኤች. አይ.ቪ/ ኤድስ የባሕሪ ጥናት የመረጃ ማቀነባበር ተግባር ተጠናቆ መረጃው ለተጨማሪ የትንተና ሥራ ለሚመለከተው አካል (ለጤና ጥበቃ ሚ/ር) ተላልፏል፡፡ ውጤቱም በአፍሪቃ አዳራሽ የጤና ጥበቃ ሚ/ር እና የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በጋራ ባዘጋጁት አውደጥናት ለሕዝብ ይፋ ሆኖአል፡፡

- በ1998 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተካሄደለት የሰው ኃይል ጥናት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

- ለመ/ቤቱ ዓመታዊ መጽሔት የሚውሉ የማኅበራዊ ሁኔታ መረጃዎች ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተሰብስበውና ተጠናቀው ለሚመለከተው ክፍል ተልኳል፡፡

- ከአሜሪካ መንግስት ጋር በመተባበር የተሠራው የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት የ(DHS) ውጤት ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡ ውጤቱም በአፍሪቃ አዳራሽ የጤና ጥበቃ ሚ/ር እና የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በጋራ ከመስከረም 28-29 ቀን 1999 ባዘጋጁት አውደ ጥናት ለሕዝብ ይፋ ተደርጓል፡፡

4. <u>የ1999 ዓ.ም የስድስት ወራት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም</u>

በ1999 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው አዳዲስ ጥናቶችን ለማከናወን በዕቅድ መያዙንና ያከናወናቸውን ሥራዎች በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ የእነዚህን ጥናቶች የፊዚካል አፈፃፀም በተመለከተ ደግሞ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ1999 ዓ.ም የፕሮጀክቶች የፊዚካል ሥራ አፈፃፀም

ተ.ቁ.	የፕሮጀክት/ የጥናት ዓይነት	ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ደረጃ	በ1998 ዓ.ም የተከናወነ	የ1999 በጀት ዓመት ዕቅድ	የስድስት ወራት		
					ዕቅድ	ክንውን	አፈፃፀም
I	የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም						
1	የግብርና ሰብል ትንበያ ጥናት	አዲስ	6.75	93.25	93.25	93.25	100
2	የግብርና ምርት ናሙና ጥናት						
	- የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን	አዲስ	6.75	93.25	50.45	44.5	88.2
	- የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ	»	6.75	93.25	59.07	53.2	90.1
	- የመሬት አጠቃቀም	»	6.75	93.25	59.07	53.2	90.1
2.1	የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች	»	6.75	93.25	74.66	70.55	94.4
2.2	የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት	»	6.75	93.25	57.95	48.25	83.3
3.	የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ	»	-	79.36	11.68	11.68	100
4.	ወቅታዊ የማምረቻ ድርጅቶች ጥናት	»	13.00	87.0	25.75	25.75	100
5	የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ጥናት	»	13.00	87.0	44.5	44.5	100
6	የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት	»	9.00	91.0	43.83	43.83	100
7	የችርቻሮና የአገልግሎት ዋጋ ጥናት	»	15.00	85.0	39.68	39.68	100
II	የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት						
1	የቆጠራ ካርታ ሥራ ማጠናቀቅ	ነባር	32,458	10,000	10,000	9,753	97.5
2	3ኛው ሕዝብና ቤት ቆጠራ ማካሄድ	አዲስ	-	65	8	8	100

5. የሜቶዶሎጂ ሥራን በተመለከተ

በዚህ የሥራ ክፍል መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው የተለያዩ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎች ለጥናት የሚያገለግሉ መጠይቆች ጥራት ወካይነታቸውን የማረጋገጥና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች ያከናውናል። በዚሁ መሠረት በ1999 የስድስት ወራት የሚከተሉት ተግበራት ተከናውነዋል።

5.1 ሳምፕሊንግ ሜቶዶሎጂ

- ለ1998 ዓ.ም የምግብ ዋስትና ጥናት የኮድ ቡክ ዝግጅት፣ የ1998 የዋናው መኸርና የበልግ ወቅት የግብርና ጥናት እንዲሁም የተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት የሜቶዶሎጂ ሪፖርት፣ ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

- የ1998 የበልግ ወቅት የግብርና ጥናት የተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት weight እና Rate ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል፡፡

- ለ1999 ዓ.ም. ግብርና ናሙና ጥናት አዲስ ለተከፈቱት ተጨማሪ ሦስት ዞኖች እና ነባር ሆነው በአዲሶቹ ምክንያት ለተከፈሉ አምስት ዞኖች አዲስ የቆጠራ ቦታዎች ምርጫ ተከናውኗል፡፡

- ለ1999 ዓ.ም. ግብርና ናሙና ጥናት ኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ የሚያገለግል ኮድ ቡክ ዝግጅት እንዲሁም weight እና Rate የማዘጋጀት ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ የሜቶዶሎጂ ሪፖርቱም ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- የ1999 ዓ.ም የቤት እንስሳት ጥናት የኤዲቲንግ ኮዲንግ ክትትልና የአካባቢ መለያ ኮዶች የእርማት ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ የአርባ ዞኖች የWeight እና Rate ሥራም ተጠናቆ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል፡፡

- የሜቶዶሎጂን ሥራ ይበልጥ ለማሻሻል የሚያስችል ሥራ ለማከናወን ልማዳዊ የአሠራር ሂደቶችን የመፈተሻ፣ ችግሮችን የመለየት ሥራና የማሻሻያ ሃሣቦች ተካተው ዝርዝር ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የበላይ አካላት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

- የቤተሰብ ገቢና ወጪ ጥናት የግብርና ናሙና ጥናቶችን በሚመለከት የተለያዩ አማካሪዎች ለማማከር ሲመጡ ሊያተኩሩባቸው የሚገባቸውን ነጥቦች ለማስገንዘብ የሚያስችል ቢጋር ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ቀርቧል፡፡

5.2 ስታንዳርድና መዛግብት አያያዝን በተመለከተ

- አጠቃላይ በስታንዳርድ ደረጃ ሊያገለግል የሚችል ለሁሉም የሥራ ክፍሎች የጋራ ፅንሰ ሃሣብና ፍችዎች በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቷል፡፡

- ለክልሎችና ለዞኖች የሚያገለግል የአካባቢ መለያና ተዛማጅ ኮዶች የተዘጋጁ ሲሆን ለICT ሥራ የሚያገለግል የVariable labeling ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

5.3 ካርቶግራፌን በተመለከተ

- ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ የ226 ወረዳዎች የቆጠራ ካርታዎችና ሌሎች ተዛማጅ ዶክመንቶች ርክክብ ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም 435 ወረዳዎች ዲጂታይዝድ የተደረጉ ሲሆን፣ በአስተዳደር ለውጥ ምክንያት በቢሮ ደረጃ የ113 ወረዳዎች የማስተካከል ሥራ ተካሂዷል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ በመጀመሪያ ስድስት ወራት 65,012 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ፎቶ ኮፒ ተደርገው ለቆጠራው ተግባር ተዘጋጅተዋል፡፡ በተጨማሪም የ39,488 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ኮድ እንዲዘጋጅላቸው ተደርጓል፡፡

- ቀደም ሲል የተሠሩ 327 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች በተለያዩ ምክንያት ግድፈት ስለታየባቸው በማስተካከል ለ58 ሠራተኞችና ለ13 ተቆጣጣሪዎች መመሪያና መግለጫውን በመስጠት ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ተደርጓል፡፡

6 የመረጃ ማቀነባበሪያ ሥራን በተመለከተ

6.1 የኤዲቲንግ ኮዲንግና ዳታ ኢንትሪ

በ1999 የዕቅድ ዘመን ስድስት ወራት ውስጥ በ1998 ዓ.ም የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባራት የተጠናቀቀላቸው የ1997 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ የ1998 የበልግ ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት፣ ወቅታዊ የICT ጥናት መጠይቆች፣ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት፣ ወርሃዊ የዋጋዎች ጥናት የምግብ ዋስትና ጥናት፣ የ1999 የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የቤት እንስሳት ጥናት፣ የሰብል ሁኔታ ግምገማ ጥናት፣ የኤዲቲንግ ኮዲንግ የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቋል፡፡ የ1998 የህዝብና ቤት የሙከራ ቆጠራ መጠይቆችና

የ1999 የሰብል ትንበያ ጥናትና የቤት እንስሳት ጥናት የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ እንዲሁም የዳታ ኢንትሪና ኪሊኒንግ ሥራ መሉ በሙሉ ተጠናቋል::

6.2 የሠንጠረዥ ዝግጅት

- በ1997 እና በ1998 የመረጃ ማሰባሰቡ ሥራ የተጠናቀቀላቸው በ1999 ዓ.ም የሰብል ትንበያ ጥናት በጠቅላላው ወደ አሥራ አራት የሚሆኑ ጥናቶች የሰንጠረዥ ዝግጅት ተጠናቋል:: እነዚህም በ1997 የሰው ሃይል ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ የ1998 የመኸር ወቅት የመሬት ስፋትና ምርት መጠን የአጠቃላይ እርሻ ሁኔታ ጥናት፣ የመሬት አጠቃቀም ጥናትና የበልግ ወቅት የመሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት፣ አጠቃላይ የእርሻ ሁኔታ ጥናት ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናትና የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወርሃዊ ጥናት፣ ወርሃዊ የዋጋዎች ኢንዴክስ ሪፖርት ተዘጋጅቷል::

- በሌላ በኩል መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች አመች በሆነ መንገድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት የ1997 የሰው ሃይል ጥናት የ1998 መኸር ወቅት የመሬት ሰፋትና ምርት መጠን ጥናት አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት፣ የመሬት አጠቃቀም መረጃ፣ የበልግ ወቅት ጥናት፣ የአምራቾችና የሸማቾች ዋጋ ጥናት፣ የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት፣ መረጃ ወደ SPSS Format የመለወጥ ሥራ ተጠናቋል::

- የ1997 የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት expenditure መረጃ ወደ SPPS እና ወደ ASCII ፎርማት የተለወጠ ሲሆን፤ የዚህ ጥናት income መረጃ ለተለያዩ ሪፖርቶች ዝግጅት የማደራጀቱ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል::

6.3 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- ለ1999 የህዝብ ቤት የሙከራ ቆጠራ መጠይቅ Scanning ሥራ ላይ ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በጋራ ለማከናወን ተችሏል::

- በ DRS ኩባንያ አማንኝነት Scan የተደረገውን መረጃ ለቅንብር ሥራ ምቹ ወደ ሆነ ፎርማት ተቀይሯል::

- Scan ተደርጐ የተዘጋጀውን መረጃ ለመጠቀም የተወሰኑ ሪፖርቶችን በማውጣት ለሚመለከተው ተላልፏል፡፡

- ለህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ የስካኒንግ ክፍልን ለማደራጀት የሚያስፈልጉ የዕቃዎች ዓይነትና ዝርዝር በማዘጋጀት ለሚመለከተው እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

7. የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን የማሻሻል ሥራን በተመለከተ

የመ/ቤቱ የICT እና የተዛማጅ ዕቃዎች ዝርዝር መረጃን ያካተተ ዳታ ቤዝ develop ተደርጐ ተጠናቋል፡፡

በዚህም ዳታ ቤዝ እንዲካተቱ የተደረጉት መረጃዎች አጠቃላይ የመ/ቤቱ የሰው ኃይል የእያንዳንዱ ኮምፒውተር ጠቀሜታና ኦፕሬቲንግ ሲስተም የኮምፒውተር ፕሪንተሮች ሞዴልና ብራንድ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

- የመ/ቤቱ ሥራ ይከናወንባቸው የነበሩ 225 ኮምፒውተሮችና 5 ፕሪንተሮች በተለያዩ ምክንያት ብልሽት ስለደረሰባቸው የብልሽቱን ክብደትና ቅለት በመፈተሽ ተገቢው ጥገናና የማስተካከል ሥራ ተካሂዶ ለሥራ ብቁ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ 256 ኮምፒውተሮች 56 ፕሪንተሮች ከመ/ቤቱ ወጭ ባሉ ባለሙያዎች በዘመናዊ መሣሪያ የአቧራ ጠረጋ ሥራ ተካሂዷል፡፡

- በመ/ቤቱ በተለያዩ ወቅት የተካሄዱ ጥናቶች በማዕከላዊ የመረጃ ማዕከል ተከማችተው የተቀመጡ ሲሆን፣በቀላሉ ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ለማድረግ ከ400 በላይ ሲዲዎች ተዘጋጅተው ለሽያጭ ቀርበዋል፡፡

- የጂኦግራፊክ ኢንፎርሜሽን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማካሄድ ዲጂታይዝድ ተደርገው የተጠናቀቁ የወረዳ ካርታዎችን በማዋሃድ የዞን ካርታ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

- በተመሳሳይ በክልል ውስጥ የሚገኙ ዞኖችንም በማዋሃድ /በመቀላቀል/ የክልል ካርታዎችን የማዘጋጀቱ ሥራ በተጓዳኝ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

- የ2004 የማህበራዊ ደህንነት ጥናትና "Ethio-info" መረጃዎችን በመጠቀም በክልልና በዞን ደረጃ አትላስ ለማዘጋጀት ተችሏል። እንዲሁም ከመስክ በGPS ተሰብስበው የመጡ መረጃዎችን በመጠቀም የ266 ወረዳዎች Coordinates ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ ተጠናቋል።

- የተቀላጠፈና አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች ለማዳረስ የትላልቅና መለስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናትና መሠረት በማድረግ በሠንጠረዥና የኢንትሪ ሪሌሽን እንዲሁም የዲያግራም ዝግጅት ተጠናቆ ዳታ ሞዴል ተዘጋጅቷል።

- የተዘጋጀው ዳታ ቤዝ በመ/ቤቱ ውስጥ ያለውን የኢንዱስትሪ data በመጠቀም ተሞክሮ አበረታች ውጤት በማስገኘቱ የኢንዱስትሪን ጥናት ዳታ ቤዝ የማዘጋጀቱ ሥራ በአጥጋቢ ሁኔታ ተጠናቋል። በሌላ በኩል ጥሬ መረጃዎችንና ሪፖርቶችን ለመጠቀም ጥያቄ ላቀረቡ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድረጅቶች እንዲሁም ለተመራማሪዎችና ተማሪዎች ተገቢው አገልግሎት ተሰጥቷል።

8. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ሥራን በተመለከተ

8.1 የሰው ሃይል አስተዳደር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በሚመለከት

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
ለአዲሱ ድርጅታዊ ማመቅር የሰው ኃይል የመደልደል ተግባር ሥራን ማዕከል ያደረገ ይሆን ዘንድ መከታተል፤	በአዲሱ ድርጅታዊ መዋቅር በተፈቀደ የሥራ መደቦች ላይ የሥራ ውጤትን ማዕከል ያደረገ የሠራተኞች ምደባን ለማካሄድ በፌደራል ሲቪል ሰርቪስና በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የወጡ መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ በመጀመሪያው ዙር የመምሪያ፣ የአገልግሎት፣ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤትና የስነ ምግባር ኃላፊዎችን በመመደብ የውሳኔ ሐሳብ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቧል። ከቡድንና ከዋና ክፍል ኃላፊነት ጀምሮ ወደታች ባሉት የሥራ መደቦች ላይም የምደባው ሥራ በመገባደድ ላይ ነው።
የሰው ኃይል መረጃ ከምፒውተራይዝ እንዲሆን መከታተል፤	የሰው ኃይል መረጃ ሙሉ በሙሉ ኮምፒውተራይዝድ የሆነ ሲሆን፤ በአሁኑ ሰዓት መረጃውን የማጥራት/የማስተካከል ሥራ እየተካሄደ ነው።
አስፈላጊ በሆኑ የሥራ መደቦች ላይ የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን፤ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የሥራ ዘርዝር /ፎርም 14/ ማዘጋጀት	በመረጃ ማቀነባበሪያ መምሪያና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማስተባበሪያ መምሪያ በተወሰኑ የሥራ መደቦች ላይ የሥራ ልምድና የትምህርት ዓይነትና ዝግጅት እንዲሁም በቴክኒክና ንብረት አስተዳደር በሾፌር የሥራ መደብ ላይ የማሻሻያ ጥያቄ ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ቀርቦ ምላሽ እየተጠበቀ ነው።
የመ/ቤቱ የሥልጠና ፖሊሲ ሲዘጋጅ መከታተል፤	መ/ቤቱ ሙሉ ትኩረት በግንቦት ወር 1999 ዓ.ም. በሚካሄደው 3ኛው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ላይ ስለሆነ ሥራው አልተጀመረም።

8.2 የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በሚመለከት

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
ከመሥሪያ ቤቱ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚፈጀውን ጊዜ፣ በምን መልክ መውሰድ እንደሚቻል እና የሚጠየቅ የክፍያ መጠን /የሚጠየቅ ከሆነ/ በመጽሔትና በቡሮሽር ማውጣት፤	የአገልግሎት አይነቶችንና የክፍያ መጠን በማሰባሰብ ሥራ ተጠናቋል። በተጨማሪም እያንዳንዱን አገልግሎት ለመስጠት የተገመተውን ጊዜ በመከራ ለማረጋገጥ መረጃው እየተያዘ ነው።
ለረዥም ጊዜ በሰነድ ተይዘው የሚገኙ ንብረቶች እልባት እንዲያገኙ መከታተል ፤	መ/ቤቱን በመልቀቅ፣ በጡረታ በመገለልና በሞት የተለዩ ሠራተኞች ለመ/ቤቱ ያስረከቡት ዕቃ ባለመሠረዙና ለመስክ ሥራ ወጪ የሆኑ ዕቃዎችም ባለመመለሳቸው ለረጅም ጊዜያት በግለሰቦች ስም ለተመዘገቡት የንብረት ሰነዶች ዕልባት ለመስጠት አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲያገኙ የተቋቋመው ኮሚቴ ጉዳዩን በዝርዝር በማጥናት የውሳኔ ሃሣብ ለማኔጅመንት አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን፤ በ2000 ተግባራዊ እንዲሆን ተወስኗል።
ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶች በተገቢው ማስወገጃ መንገድ እንዲወገዱ ክትትል ማድረግ	ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶች፣ መኪናዎችን፣ ሞተር ሳይክሎችን የመጠይቅ ወረቀቶችን... ወዘተ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ለማስወገድ የገማች ኮሚቴና የአስወጋጁ ኮሚቴ አባላት የየድርሻቸውን ሥራ በማከናወን ከተሽከርካሪዎች በስተቀር ሌሎች ዕቃዎች በመወገድ ላይ ሲሆኑ የመኪናዎች ግምትም እየተካሄደ ይገኛል።
የመ/ቤቱ ራዕይ፣ የተልዕኮ መግለጫና ዓላማዎች እንዚሁም ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ በነበረው የቢሮ አቅጣጫ አመልንች ላይ ማስተንከያ በማድረግ በካሜራ ላይ መጻፍ፤ይህንኑ ለብሮሽር ማውጣት	በመ/ቤቱ እየተረገ ባለው የቢሮ ድልድል ሽግሽግ አለመጠናቀቅ ተግባራዊ አልሆነም።

8.3 የበላይ ሥራ አመራር ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በተመለከተ

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
የአሠራር ማሻሻያ ጥናት የሚያካሂዱ የሥራ ክፍሎች አፈጻጸማቸው በበላይ አካል እንዲገመገም መከታተል፤	በ1999 ዓ.ም የ BPR ሥራ ለመከናወን በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም በመ/ቤቱ ከሚካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ ግዙፍ ሥራ ጋር ለመተግበር እንደማይችል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስተያየት ስለሰጠበት መ/ቤቱም አስተያየቱ ተገቢ መሆኑን አምኖበት ሥራው ለሚቀጥለው በጀት ዓመት እንዲሸጋገር ተደርጓል።
አመራር ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ቅሬት ሲቀርብ ለግልጽ ውይይት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣	ባለፉት ስድስት ወራት የቀረበ ቅሬታ ባይኖርም፣ ሥራው ዓመቱን በሙሉ የሚከናወን በመሆኑ ከተከሰተ ተፈፃሚ ይደረጋል።

8.4 የሥነ ምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በሚመለከት

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
ሥነምግባር መርሆች ለእይታ አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ መሰቀሉን መከታተል፤	የስነ-ምግባር መርሆችን ጽሁፍ እና በፕላስቲክ የመለበድ ሥራ ተጠናቆ ጽሁፉን በፍሬም መስተዋት ውስጥ ለማስቀመጥ በማስፈለጉ እየተሠራ ይገኛል፡፡
የተለያዩ ጥቆማዎችን በመቀበል ለማኔጅሜንት የውስኔ ሃሳብ ማቅረብ፤	በአንድ የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት በተከሰተው የመንግሥት ተሽከርካሪን ለግል ገቢ ማስገኛ የማዋል ጥቆማን ለማጣራት የሚመለከተው የባለሙያ ቡድን በቦታው በመገኘት ጉዳዩን በማጣራት ሪፖርት ለበላይ ኃላፊ እንዲቀርብ ተደርጐ ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ተመርቷል፡፡ በሌላ በኩል ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የነበራቸው ሁለት የኮንትራት ቅጥር ሾፌሮች ከሥራ እንዲሰናበቱ ሲደረግ፣ በሌላ ቅ/ጽ/ቤት በቀረበ የመንግሥት መኪና ያለ ግባብ የመጠቀም ጥቆማ ጉዳዩ ተጣርቶ ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነ የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ተሰጥቷል፡፡
የሥነ-ምግባር ደንብ ዝግጅት መጠናቀቅ ከመታተል፤	በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀውን የሥነ ምግባር ደንብ ለማጠናቀቅ የሥነ-ምግባር መኮንን ከፌዴራል ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር ግንኙነት አድርጐ ሀገር አቀፍ የሥነ ምግባር ደንብ እየተዘጋጀ ነው በመባሉ ለጊዜው የዝግጅቱ ሥራ እንዲቆም ተደርጓል፡፡
የተለያዩ ጥቆማዎችን በመቀበል ለማኔጅመንት የውሣኔ ሣሣብ ማቅረብ፤	አንድ የቅ/ጽ/ቤት የአስተዳደርና ሂሣብ ኃላፊ የመንግሥት መኪናን ለግል ገቢ ማስገኛ የማዋል ጥቆማን በማጣራት ሪፖርት ለበላይ ኃላፊ ቀርቦ ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ተመርቶዋል፡፡ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ድርሻ ያላቸው ሁለት ኮንትራት ቅጥር ሾፌሮች ከሥራ እንዲሰናበቱ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም አንድ የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ላይ በቀረበ የመንግሥት መኪና አላግባብ የመጠቀም ጥቆማ ላይ የማጣራት ሥራ ተከናውኖ ከጥፋቱ እንዲታረም በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡

8.5 <u>ሌሎች በዕቅድ ሳይያዙ የተከናወኑ ሥራዎች</u>

- የኤጀንሲው መ/ቤት የፋይናንስ መምሪያና የኦዲት መምሪያ የሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች ስለሌሏቸው በባለሙያዎች ለማስያዝ ማስታወቂያ ወጥቶ በተሰጠው ፈተና ብልጫ ያገኙት ባለሙያዎች ሥራ ጀምረዋል፡፡

- በሌላ በኩል በመ/ቤቱ ፋይናንስ በማንቀሳቀስ፣ በማወራረድና ሪፖርት በማዘጋጀት ረገድ በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ

ኃላፊዎችና የማኔጅመንት አባላት በተገኙበት በየሳምንቱ አንድ ቀን በመወያየት አያሌ ችግሮችን ለመፍታት ተችሏል፡፡

- መሥሪያ ቤቱ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመትና ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በማቅረብ ረገድ ሲያጋጥሙት የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት ያልተማከለ የሂሳብ አሠራር ስርዓት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ለመተግበር ወስኗል፡፡ የማሻሻያ ስርዓቱም በመጀመሪያ በሰባት ቅ/ጽ/ቤቶች ከጥር 1/1999 ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በሌሎቹ 18 ቅ/ጽ/ቤቶች ደግሞ ከሐምሌ 1/1999 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ለሥራው ውጤታማ መሆንም ለ25ቱም ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ለ18 የአስተዳደርና ሂሳብ ኃላፊዎች የ 2 ቀናት፣ ለሁሉም ኦዲተሮች፣ ሂሳብ ሠራተኞች እና ለ 7 የአስተዳደርና ሂሳብ ሠራተኞች የ9 ቀናት የአቅም ማሳደጊያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የቅ/ጽ/ቤቶች የሥልጣን ውክልናን ደረጃ በደረጃ ለማሣደግ እየተደረገ ባለው እንቅስቃሴ የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥርና ስንብት አፈፃፀምን ወደ ዋናው መ/ቤት በመላክ የይሁንታ መልስ መጠበቅ ሳያስፈልግ በራሣቸው እንዲያጠናቅቁ ውክልና ተሰጥቷል፡፡

9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት ሥራን በተመለከተ

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
ልሣነ መስኡን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣	የመ/ቤቱ ልሳን የሆነው ልሳነ ማስኡ ቅጽ 06 ቁጥር 07 መጽሄት 2,000 ኮፒ ታትሞ ከመ/ቤቱ ጋር ግንኙነት ላላቸው አካላት ተሰራጭቷል፡፡
የ1999 መልካም ምኞት መግለጫዎችን ማዘጋጀት፣ ማሳተምና ማሰራጨት፣	5,000 የግድግዳ የቀን መቁጠሪያዎች እንዲሁም 10,000 ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው የኪስ የቀን መቁጠሪያዎች ታትመው ተሰራጭተዋል፡፡
የመ/ቤቱን ጥናቶች አስመልክቶ በመገናኛ ብዙኃን መግለጫዎችን መስጠት፣	የመ/ቤቱን የ1999 የሕዝብና ቤት ቆጠራና የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ፣ የህዝብና ቤት ቆጠራን መረጃ በስካኒንግ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም እንዲቻል የተካሄደውን ሥልጠና፣ የ1999 የግብርና ናሙና ጥናትን፣ እንዲሁም የ1998 የበልግ ወቅት ሰብል ምርት ጥናት ውጤትን በከተሞች የሥራ ስምሪት ሁኔታን በተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዝንና በጋዜጦች በሥራ ኃላፊዎች የተሰጡ መግለጫዎች የዜና ሽፋን እንዲያገኙና ለህብተሰቡ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ጥረት ተደርጓል፡፡

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
በመ/ቤቱ የተዘጋጅ የጥናት ሪፖርቶችን በሽያጭ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣	1,645 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች በብር 38,702.10 ሽያጭ የተፈጸመ ሲሆን፤ 315 በሲዲ (CD) የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ሪፖርቶች በብር 7,349 ተሸጠዋል፡፡ እንዲሁም በብር 30,200 ጥሬ መረጃ ተሸጧል፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ኤጀንሲው በሽያጭ ሊያቀርብ ካቀደው ብር 50,000 ጋር ሲነፃፀር 152.5 በመቶውን አከናውኗል፡፡ ክንውኑ ከአጠቃላይ ዕቅዱ ሊበልጥ የቻለው የመረጃ ፈላጊዎች ቁጥር ከዚህ ቀደም ከነበረው እየጨመረ መሆኑና ድጋሚ ሕትመት በመደረጉ እንዲሁም በጥሬ መረጃ ሽያጩም ከታቀደው በላይ መከናወኑ ነው፡፡
በመ/ቤቱ የተዘጋጅ የጥናት ሪፖርቶችን በነጻ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣	በመ/ቤቱ የተዘጋጁና ግምታቸው ብር 58,892 የሆነ 4,431 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች ለመንግሥት፣ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ለምርምር ማዕከሎች በነፃ ተሠራጭተዋል፡፡
ዓመታዊ መጽሔቶችንና መጽሐፎችን ማስመረጥና ማስገዛት፣	በ1999 የዕቅድ ዘመን መጽሐፍ እንዲገዛላቸው ከመ/ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች በሚመጡ ጥያቄዎች መሠረት ተጨማሪ መጻሕፍትን ለመግዛት የፍላጐት መጠየቂያ ቅጽ ለሁሉም የሥራ ክፍሎች ተልኮ ቅጾቹ እንዲሞሉ ተደርጐ በአሁኑ ሰዓት የግዥው ሂደት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡
የመ/ቤቱን ቤተመፃህፍት ለተጠቃሚዎች ክፍት ማድረግና በተጠቃሚዎች የሚቀርቡ አገልግሎቶችን እንዲያከናውን ብቁ ማድረግ፣	የመ/ቤቱ ቤተ መጻህፍትም ለመ/ቤቱ ሠራተኞችና ከውጪ ለሚመጡ ተገልጋዮች ያልተቋረጠ የንባብ፣ የትውስትና የመረጃ አቅርቦት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
ዜና ማስኤን መጽሔት ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣	የመ/ቤቱ ዜና መጽሄት ማስኤ ቅጽ 05 ቁጥር 01 መጽሔት 1,500 ኮፒ ታትሞ ተሠራጭቷል፡፡

- ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ 202 የመ/ቤቱን ሪፖርቶች በመረከብና 53 ልዩ ልዩ የውጭና የአገር ውስጥ ህትመቶችን በስጦታና በልውውጥ በማሰባሰብ ቤተ መጻህፍቱን ለማጠናከር ተሞክሯል፡፡

- በቤተ መጻህፍቱ ውስጥ ለውጭ ተገልጋዮች የፎቶ ኮፒ አገልግሎት በመስጠት ብር 1,175 ገቢ ተገኝቷል፡፡ "ኢትዮጵያ" ለተሰኘውና በማስታወቂያ ሚኒስቴር በሚዘጋጀው ዓመታዊ መጽሔት ላይ የሚወጣ የመ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ተልኳል፡፡

10. የኦዲት ሥራን በተመለከተ

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
የ1998 በጀት ዓመት ገቢና ወጪ ሂሣብ ምርመራ ማድረግና ለበላይ አካል ሪፖርት ማቅረብ፣	የ1998 የመ/ቤቱን የገንዘብ ቤት ካዝና /ሳጥን/ ሂሳብ ምርመራ ተደርጐ ብር 9350.78 ፈስስ እንዲሆን በማድረግ ሪፖርቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተላልፏል፡፡
የመ/ቤቱ ገንዘብ ቤት በየወሩ የሂሣብ ምርመራ ማድረግና ሪፖርት ማቅረብ፣	የሐምሌና የነሐሴ ወር የ1998 ዓ.ም እና የመስከረም ወር 1999 ዓ.ም የመ/ቤቱ የሳጥን /ካዝና/ ሂሣብ ምርመራ ተደርጐ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ቀርቧል፡፡
የአገልግሎቱን የሩብ ዓመት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል ማቅረብ	የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት የተዘጋጀ ሲሆን፤ የሁለተኛውን ሩብ ዓመት ሪፖርት ለማዘጋጀት የፋይናንስ መምሪያ ሂሣቡን ዘግቶ ሪፖርት ባለማቅረቡ ማጠናቀቅ አልተቻለም፡፡

- የመ/ቤቱን ሠራተኞች የሰዓት ፈርማ ምርመራ ተደርጐ ሪፖርት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቧል፡፡

- የ1998 የመ/ቤቱን የዕቃ ግምጃ ቤት ቆጠራ ተካሄዶ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

- የ1997 በጀት ዓመት ሂሣብ ምርመራ ተጠናቆ ሪፖርቱ እየተዘጋጀ ያለ፣ ሲሆን፣ የ1998 በጀት ዓመት ሂሣብ ዝርዝር ምርመራና በመዝገብ ላይ ከተመዘገበው ጋር እየተመሳከረ ይገኛል፡፡

- የ1999 በጀት ዓመት ሂሣብ ዝርዝር ምርመራ በመደረግ ላይ ያለ ሲሆን፣ የ1998 በጀት ዓመት ሂሳብ ዝርዝር ምርመራ የተጀመረ ቢሆንም የውጪ ኦዲተሮች አብዛኛውን የሂሳብ ማስረጃዎች በመያዛቸው ሥራው ለጊዜው ተቋርጧል፡፡

- ለቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲተሮች በኦዲት ማንዋል፣ በሞዴል፣ በቋሚና ጊዜያዊ ፋይሎች ላይ ያተኮረ ሥልጠና ለ9 ቀናት ተሰጥቷል፡፡

11 የሕግ አገልግሎት ሥራን በተመለከተ

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
...ሙ/ቤቱ የተቀጠሩ ሠራተኞች የመንግሥት ...ንብረትን ለግል ጥቅም አውለው ...ኑ ክስ መመስረትና ገንዘቡን ማስመለስ፤	ሙ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ጥናቶች ላይ ተቀጥረው ሲሰሩ የነበሩ ሁለት ሠራተኞች በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን በመልቀቃቸው ለሥራ የወሰዱትን ብር 1,362 እንዲሁም አንድ የሂሣብ ካልኩሌተር ለሙ/ቤቱ ተመላሽ እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡
...ሙ/ቤቱ በውጪና በአገር ውስጥ ...ስተምሯቸው የተማሩበትን ያህል ሙ/ቤቱን ...ግለግሉ የሚለቁ ሠራተኞችን የተማሩበትን ...ገንዘብ እንዲከፍሉ በፍርድ ቤት ጉዳያቸው ...ክታተል፤ ገንዘቡን ማስመለስ፤	ሙ/ቤቱ አስተምሯቸው በገቡት ውል መሠረት ያላገለገሉ አንድ ባለሙያ ለትምህርት ወጪ ብር 9,366.40 እንዲከፍሉ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዋናውን ገንዘብ፣ ወለድና ኪሣራ ሙሉ በሙሉ ገቢ እንዲያደርጉ ሲሆን፤ ቀሪውንም በጥር ወር እንዲከፍሉ ቀጠሮ ተይዟል፡፡
...ተለያዩ ሁኔታዎች በሌሎች ግለሰቦች ...ተበደሩ የሙ/ቤቱን ንብረትና ገንዘብ ...ማስመለስ በፍርድ ቤት ጉዳያቸወን ...ክታተል፤	ሶስት የሙ/ቤቱ ሠራተኞች በተለያዩ ምክንያት ያጐደሉትን የመንግሥት ገንዘብ እንዲከፍሉ በጠቅላላው በብር 73,449.30 ክስ ተመስርቶ በዚህ ስድስት ወራት ውስጥ ክትትል የተደረገበት ሲሆን ጉዳዩ በቀጠሮ ላይ ነው፡፡
...1999 በጀት ዓመት በፊት የተጀመሩና ውሣኔ ...ሳገኙ ክሶችን በፍርድ ቤት መከታተል፤	ከ1999 ዓ.ም. በፊትና በኋላ ሙ/ቤቱ የጉዳት ካሳ እዲከፍል በማለት በተለያዩ ፍ/ቤቶች ክስ ባቀረቡት ላይ በዚህ ስድስት ወራት በተደረገው ክትትል የብር 42,960 ክስ ሙ/ቤቱ በነፃ ተሰናብቷል፡፡
...ዋናው ሙ/ቤትና ከቅ/ጽ/ቤቶች የሚነሱ የህግ ...ጉዳዮች ላይ ህጐችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና ...መመሪያዎችን በማገናዘብ የተሟላ የሕግ ...ስተያየት መስጠት፤	ጥያቄው በሚቀርብበት ጊዜ አስፈላጊው ድጋፍ እየተሰጠ ይገኛል፡፡
...ሙ/ቤቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች ...ሙ/ቤቶች ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር ለሚደረጉ ...ግንኙነቶች ህጋዊ ውሎችን ማዘጋጀት፤	ጥያቄው በሚቀርብበት ጊዜ አስፈላጊው ድጋፍ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

- ከሐምሌ 1997 ዓ.ም. ጀምሮ የተቋረጠ የበረሃ አበል ይከፈለን በማለት በተለያዩ ፍ/ቤቶች ባቀረቡት ክስ ላይ በዚህ ስድስት ወራት ውስጥ በተደረገው ክትትል ጉዳዩን ሲመለከት የነበረው ፍ/ቤት ሙ/ቤቱን በነፃ አሰናብቶታል፡፡

- በመ/ቤቱ ላይ የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ የመሠረተው የብር 5,649.98 የፍትሐብሔር ክስ በተደረገው ክትትል ፍ/ቤቱ ክሱን በይርጋ ቀሪ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶ መ/ቤቱን በነፃ አሰናብቶታል፡፡

12 የፕላንና ፕሮግራም ሥራን በተመለከተ

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
የ1999 በጀት ዓመት የካፒታል በጀት ወርሃዊ የፋይናንስ ፍላጐት ማዘጋጀትና ለበላይ አካል ማስተላለፍ፤	በ1999 በጀት ዓመት መ/ቤት ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክት የተመደበውን የካፒታል በጀት ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመሆን ወርሃዊ የፋይናንስ ፍላጐት በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡
የበጀት ዕጥረት በሚታይባቸው የወጪ መደቦችን በመለየትና ዝውውር ማዘጋጀት፤	መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ሁለት የካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ በተፈቀዱ የተለያዩ ፍዕሶች እጥረት የታየባቸውን በመለየት የዝውውር ጥያቄ ለሚመለከተው ክፍል አቅርቦ ዝውውሩ ተፈጽሟል፡፡
የመ/ቤቱን አጠቃላይ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል ማስተላለፍ፤	የ1999 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርትን እንዲሁም የ1998 ዓ.ም ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ አድርጓል፡፡

13 የሰው ሃብት ሥራ አመራር ሥራን በተመለከተ

13.1 የሰው ኃይል

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
ለመዋቅር ድልድል የቋሚ ሠራተኞች ማህደር በማጣራት መረጃዎችን መሰብሰብ፤	በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሁሉም ቋሚ ሰራተኞች ማህደር የማጣራት ስራ ተከናውኗል፡፡
ለመዋቅር ድልድል የ9 ወር የቋሚ ሠራተኞች ምዘና ውጤት ተከታትሎ መረከብና ማያያዝ፤	በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሁሉም ቋሚ ሰራተኞች የዘጠኝ ወር ምዘና ስራ ተከናውኗል፡፡
በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የቋሚ ሠራተኞች አዲስ ቅጥር መፈፀም፤	የሃያ ቋሚ ሰራተኞች ቅጥር ተካሂዷል፡፡
በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የኮንትራት ሠራተኞች መቅጠር፤	የ2,492 ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል፡፡
ዓመታዊ የሰው ኃይል አስተዳደር ተግባራትና ማከናወን፤	የመ/ቤቱን ቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር፤ ዝውውር፤ ጡረታ፤ የዓመት ዕረፍት.. ወዘተ ሥራ ተከናውኗል፡፡

የሰው ኃይል ሁኔታ

ተ ቁ	አጠቃላይ ሁኔታ	የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ		
		ቋሚ	ኮንትራት	ድምር
1	በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ	1,662	1,326	2,988
2	አዲስ የተቀጠሩ	20	2,492	2,512
5	ምተለያዩ ምክንያት ሥራ የለቀቁ	(38)	(1,281)	(1,319)
6	በጡረታ የተገለሉ	(2)	-	(2)
7	በሞት የተለዩ	(9)	-	(9)
8	አሁን ያለው የሰው ኃይል	1,633	2,537	4,170

ማስታወሻ፣ ኮንትራት ሠራተኞችን በሚመለከት ሥራ የለቀቁ የሚለው ኮንትራታቸውን ጨርሰው የተሰናበቱ መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባዋል፡፡

14 የፋይናንስ ሥራን በተመለከተ

በ1999 በጀት ዓመት የኤጀንሲው መ/ቤት ለሚያካሂደው ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 31,104,800.00፣ ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት ብር 277,733,000.00 እና ለመደበኛ በጀት ብር 18,318,900.00 በድምሩ ብር 327,156,700.00 ተፈቅዷል፡፡

ሀ. መደበኛ በጀት

ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው መደበኛ በጀት ውስጥ ለደመወዝ ብር 14,911,500 ለሥራ ማስኬጃ ብር 3,407,400 የተመደበ ሲሆን፣ ከሐምሌ 1/1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30/1999 ዓ.ም ድረስ የመደበኛ ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነው ብር 9,553,570 ሲሆን በሥራ ላይ የዋለው ደግሞ ብር 8,455,680 ነው፡፡ አፈፃፀሙም በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃፀር 88.5 % ነው፡፡

ለ. የካፒታል በጀት

የኤጀንሲው መ/ቤት በ1999 ዓ.ም ለሚያካሂደው ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 31,104,800.00 የተመደበ ሲሆን ከሐምሌ 1/1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30/1999 ዓ.ም ድረስ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነው ብር 23,697,050 ሲሆን ወጪ የሆነው ደግሞ ብር 19,826,911 ነው፡፡

በስድስት ወራት ውስጥ ገቢ የሆነው ወጪ ከተደረገው ጋር ሲነፃፀር 83.7 በመቶ ሲሆን ለዓመቱ ከተመደበው ጋር ደግሞ 63.7 በመቶ ይሆናል፡፡

እንዲሁም ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ብር 277,733,000 የተመደበ ሲሆን፤ ከሐምሌ 1/1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30/1999 ዓ.ም ድረስ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነው ብር 22,298,898 ሲሆን ወጪ የሆነው ደግሞ ብር 9,430,967 ነው፡፡ በመጀመሪያው ስድስት ወራት ገቢ የሆነው ወጪ ከተደረገው ጋር ሲነፃፀር 42.3 በመቶ ሲሆን፤ ለዓመቱ ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 3.4 በመቶ ይሆናል፡፡ በስድስት ወራቱ የተከናወነው ከታቀደው አነስረኛ የሆነው በተለይ ለጽ/መሣሪያ፣ ለሕትመት፣ ለትምህርትና ቅስቀሳና ለቆጠራው የሚውሉ የተለያዩ ወጪዎችን መ/ቤቱ በዕርዳታ ባገኘው ገንዘብ እንዲሸፈን በማድረጉ ሲሆን፤ ለዚህ ፕሮጀክት የተመደበው በጀት በአብዛኛው ተግባራዊ የሚሆነው ለክልሎች በየካቲት ወር 1999 ከተሰራጨ በኋላ በግንቦት 1999 ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ዝርዝሩም በሚቀጥሉት ሠንጠረዦች ላይ ቀርቧል፡፡

የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

ተ.ቁ	የበጀት አጠቃቀም	ለ1999 በጀት ዓመት ከመንግሥት ግ/ቤት የተፈቀደ	ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ ገቢ የሆነ	ገቢ ከሆነው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ	አፈፃፀም 04 ከ 03 በመቶኛ
	01	02	03	04	05
1	ለመደበኛ በጀት	18,318,900	9,553,057	8,455,680	88.5
	6111	14,911,500	7,474,200	7,273,874	97.3
	6121	90,300	37,200	36,265	97.5
	6131	894,700	477,360	438,560	98.0
	6211	195,600	195,600	154,763	97.1
	6212	200,000	200,000	20,427	10.2
	6217	157,300	78,660	14,099	17.8
	6218	43,000	43,000	756	1.8
	6219	10,000	-		-
	6231	15,000	8,500	544	6.4
	6232	10,000	6,000	637	10.6
	6233	18,200	9,120	3,931	43.0
	6241	111,000	83,250	2,531	3.0
	6243	80,000	40,000	5,116	12.8
	6244	20,000	20,000	12,936	64.7
	6252	584,400	292,200	292,186	99.9
	6253	50,000	25,000	9,382	37.5
	6254	6,000	3,600	675	18.8
	6255	12,000	4,800	2,240	46.7
	6256	52,400	26,220	10,031	38.3
	6257	124,000	62,040	50,966	82.2
	6258	439,600	219,840	91,589	41.7
	6259	339,000	16,980	12,580	74.1
	6271	10,000	10,000	100	1.0
	6314	250,000	250,000	21,492	8.6

የካፒታል በጀት አጠቃቀም I

ተ.ቁ	የበጀት አጠቃቀም	ለ1999 በጀት ዓመት ከመንግሥት ግ/ቤት የተፈቀደ	የተዛወረ በጀት		የተስተካከለ በጀት	ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ ገቢ የሆነ	ገቢ ከሆነው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ	አፈፃፀም በ07 እና 06
			+	-				
	01	02	03	04	05	06	07	08
2	የካፒታል							
	ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም	31,104,800	2,756,000	2,756,000	31,104,800	23,697,050	19,826,911	83.7
	6113	12,789,500		2,236,000	10,553,500	8,242,500	6,663,243	80.8
	6114	3,123,200		520,000	2,603,200	2,149,700	1,625,344	75.6
	6123	880,900			880,900	550,900	447,635	75.8
	6211	400,000			400,000	400,000	14,740	3.7
	6212	420,000			420,000	360,000	137,523	38.2
	6213	300,000			300,000	300,000	31,784.70	10.6
	6217	2,300,000			2,300,000	1,496,200	1,400,416	93.6
	6231	3,500,000	1,500,000		5,500,000	3,131,400	3,894,831	124.4
	6232	209,500	300,000		509,500	187,700	327,364	174.4
	6241	2,800,000			2,800,000	2,427,400	1,551,578	63.9
	6243	100,000			100,000	41,000	937	2.3
	6252	652,600	60,000		712,600	343,700	358,438	104.3
	6254	1,090,100			1,090,100	1,090,100	919,631	84.4
	6255	85,000			85,000	49,700	32,650	65.7
	6256	50,000			50,000	25,000	16,381	65.5
	6257	44,000	20,000		64,000	21,000	22,745	108.3
	6258	400,000			400,000	150,000	104,841	69.9
	6259	60,000	20,000		80,000	30,000	33,200	110.6
	6271	1,900,000	856,000		2,756,000	2,700,750	2,273,630	84.2

የካፒታል በጀት አጠቃቀም II

ተ.ቁ	የበጀት አጠቃቀም	ለ1999 በጀት ዓመት ከመንግሥት ግ/ቤት የተፈቀደ	የተዛወረ በጀት		የተስተካከለ በጀት	ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ ገቢ የሆነ	ገቢ ከሆነው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ	አፈፃፀም በ07 እና 06
			+	-				
	01	02	03	04	05	06	07	08
3	የካፒታል							
	የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት	277,733,000	26,834,500	26,234,500	277,733,000	22,298,898	9,430,967	42.3
	6113	6,978,900		1,200,000	5,778,900	3,642,900	2,048,685	56.2
	6114	8,594,900			8,594,900	1,005,000	592,294	58.9
	6123	383,700			383,700	242,420	81,156	33.5
	6212	2,607,300			2,607,300	2,559,800	39,569	1.5
	6213	3,900,800			3,900,800	1,655,340	4,319	0.3
	6217	7,800,000			7,800,000	1,152,000	815,774	70.8
	6218	262,000			262,000	262,000	293	0.1
	6231	114,000,000	1,200,000		115,200,000	5,111,910	4,079,509	79.8
	6232	387,000	448,500		835,500	92,200	84,943	92.1
	6241	4,200,000			4,200,000	2,479,240	1,134,562	45.8
	6243	825,500		400,000	425,500	209,000	3,836	1.8
	6251	1,850,000			1,850,000	1,540,000	-	-
	6252	448,500		448,500	448,500	-	-	-
	6253	66,000			66,000	66,000	28,955	43.9
	6254	3,500,000			3,500,000	598,000	320,431	53.6
	6255	439,200	400,000		839,200	24,000	6,600	27.5
	6256	254,700			254,700	45,000	5,157	11.5
	6257	34,500			34,500	-	-	-
	6258	1,200,000			1,200,000	107,640	66,410	61.7
	6271	9,5000,000	24,186,000		119,186,000	1,292,900	11,700	0.09
	6211	-	600,000		600000	-	-	-
	6313	25,000,000		24,186,000	214,000	213,548	106,774	50.0

15 የቴክኒክና ንብረት አስተዳደርን ሥራ በተመለከተ

የስድስት ወራት ዕቅድ	ክንውን
የ1999 ዓመታዊ የደንብ ልብስ ግዥ ማከናወን፣	በዋናው መ/ቤትና በስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸውን የሠራተኞች ቁጥር በማጣራት ጨረታው በጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጐ ጨረታውም ተከፍቶና አሸናፊው ተለይቶ ከካፖርት በስተቀር ግዥው ተፈፅሞ ለተጠቃሚዎች በመሠራጭት ላይ ይገኛል፡፡
የ1999 ዓመታዊ የጸ/መሣሪያ፣ የሕትመትና ቋሚ ዕቃዎችና ሌሎች ግዥዎችን ማከናወን፣	የጫማ፣ የጐማ፣ የኮምፒውተር፣ የጽሕፈት መሳሪያ፣ ካርቶን ግዥ፣ እንዲሁም የጠረጴዛ፣ ወንበርና መደርደሪያ ለመግዛት የጨረታ ዶኩመንት ተሸጦ አሸናፊው ተለይቶ ግዥውን በመፈጸም ዕቃዎቹ ገቢ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡ በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት በመንግሥት በተፈቀደ ብር 4.5 ሚሊዮን በጀት ለሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ተግባር የግዥ ሂደት የተጀመረ ቢሆንም መ/ቤቱ ባደረገው ጥረት በረጂ ድርጅቶች አማካይነት የብር 3.8 ሚሊዮን ግዥ ወይም ከታቀደው 86.0 በመቶ የተከናወነ ሲሆን፤ የብር 1.5 ሚሊዮን አገልግሎትና ግዥዎች ሂደት ደግሞ በሚቀጥሉት ወራት ይፈፀማል፡፡
ወርሃዊ የስልክ፣ የመብራት፣ የውሃና ሌሎች ክፍያዎችን መፈፀም፣	የቤት ኪራይ፣ የውሃ፣ የመብራት ፍጆታን ቢሉን በመመልከትና በማጣራት ክፍያው ተፈጽሟል፡፡
የኮምፒውተር፣ የፕሪንተር፣ የሂሳብ መኪናዎችና ሌሎች የማተሚያ መሣሪያዎችን ማስጠገን	የኮምፒውተር ፕሪንተር ጥገናና PBX ግዥ ለመፈጸም የጨረታ አሸናፊው ተለይቶ በአሁኑ ሰዓት የጥገና ሥራው በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

- ለመ/ቤቱ የአትላስ ሕትመት ሥራ በጨረታ ወጥቶ ከአሸናፊውን ድርጅት ጋር ውለታ በመዋዋል ሥራው በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

- የመ/ቤቱን ሥራ በተገቢው መንገድ ለማካሄድና ለማፋጠን የቢሮ ዝውውርና የሽግሽግ ሥራና የቀድሞው የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ንብረት ወደዋናው መ/ቤት የማዛወርና የማሸጋሸግ ሥራ እየተካሄደ ነው፡፡

- ከሐምሌ 1/1998 ጀምሮ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ተካሄዶ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል፡፡

- ከሐምሌ 1/1997 እስከ ሰኔ 30/1998 ድረስ ለተለያዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የተላኩ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ለመድረሳቸው ዝርዝሩ ለ25 ቅ/ጽ/ቤቶች ተሠራጭቶ መረጃዎች ተሰብስበው በመመርመር ላይ ይገኛል፡፡

- ለመ/ቤቱ አገልግሎት ለሚውሉ የተለያዩ ዕቃዎች ማከማቻ ለሚሠራው መጋዘን በወጣው ጨረታ መሠረት በአሸናፊው ኮንትራክተር የመጋዘኑ ግንባታ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

- መ/ቤቱ ሲጠቀምባቸው የኖሩና አሁን ግን ከአገልግሎት ውጭ የሆኑትና የሚወገዱ ዕቃዎችን ለማስወገድ በዋጋ ገማችና በአስወጋጅ ኮሚቴ በጋራ በተደረሰው ስምምነት ዕቃዎቹን ለማስወገድ ቅድመ ሁኔታዎች ተጠናቀዋል፡፡

15.1 <u>ትራንስፖርትና ጥገና</u>

- ለመ/ቤቱ አገልግሎት የሚሰጡ የሁሉም ተሽከርካሪዎች የቅድመ ምርመራ ሥራ ተካሄዶ በዋናው መ/ቤት የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ምርመራ ተደርጓል፡፡ በመስክ ሥራ ላይ እያሉ በብልሽት ቆመው የነበሩ 4 ተሽከርካሪዎች በመ/ቤቱ የቴክኒክና ንብረት ባለሙያዎች ተጠግነው ለሥራ ብቁ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም 23 የሚሸጡ ተሽከርካሪዎች የቅድመ ሁኔታዎች ሥራዎች ተጠናቆ ለሽያጭ በመንገድ ትራንስፖርት መ/ቤት በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ፡፡

- የሁለት ሞተር ሳይክሎችና የ50 ስቴሽን ዋገን የመስክ ተሽከርካሪዎች ሊብሬና ታርጋ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

- በሌላ በኩል በዚህ ስድስት ወራት ውስጥ 14,338 ሊትር ቤንዚን፣ 17155 ሊትር ናፍታ፣ 253 ሊትር ዘይት፣ 14 ሊትር የባትሪ ውሃ የዋናው መ/ቤት

ተሽከርካሪዎች እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፤ ለተሰጠው አገልግሎትም ክፍያው ለማደያዎች በወቅቱ እንዲከፈል ተደርጓል፡፡

16 የሕትመት ሥራን በተመለከተ

በ1999 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት ውስጥ ልዩ ልዩ የሕትመት ውጤቶች፤ መጠይቆች፤ መመሪያዎች የጥናት ሪፖርቶች፤ የመቀስቀሻ በራሪ ወረቀቶች፤ ካርታዎች የአስተዳደራዊ ደብዳቤዎች፤ ቅጾች፤ ደክመንቶች የሂሳብ ሰነዶችና ሌሎችም የተጠየቁ የሕትመት ሥራዎች በ52,069 ጥራዞችና በ8,598,845 ገጾች ታትመዋል፡፡

17 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

17.1 የሴቶች ጉዳይን በሚመለከት

- መ/ቤቱ ከዚህ በፊት በነበረው መዋቅር የሴቶችን ጉዳይ የሚመለከት የሥራ ክፍል አልነበረውም፡፡ ሆኖም አዲሱ መዋቅር ላይ የሥራ ክፍሉ እንዲኖር በመደረጉ መዋቅሩ ተጠናቆ ሠራተኞች ለሥራ ክፍሉ በቋሚነት እስኪመደቡ ድረስ ጊዜያዊ የሴቶች ጉዳይ መምሪያ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- ይህ የተቋቋመው መምሪያም በመዋቅሩ መሠረት የሚመደቡ የክፍሉ ሠራተኞችን ሊያሠራ የሚችል የዓመቱን የሥራ ዕቅድና መረሃ-ግብር አዘጋጅቷል፡፡

- ከሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተላከ አንድ መጠይቅ ተሞልቶ ለጠያቂው መ/ቤት ተልኳል፡፡

- የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን አጠቃላይ ዕቅድ ለማዕደቅ በተደረገ የግማሽ ቀን ሴሚናር ላይ መ/ቤቱ ተሣትፎ አድርጓል፡፡

- የመ/ቤቱን የሴቶች ጉዳይ የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎችን ለጠያቂዎቹ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

17.2 የኤች. አይ .ቪ. /ኤድስን በሚመለከት/

- በአስፈፃሚ መ/ቤቶች የራሣቸው /የኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ መከታተያ ግብረሃይል እንዲያቋቁሙ በመንግሥት በተሰጠ መመሪያ መሠረት

በኤጀንሲው ውስጥ መመሪያው በሚያዘው መሠረት አንድ ግብረ-ሃይል ተቋቁሟል፡፡

- ይህ ግብረ-ሃይል የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስን በተመለከቱ ተግባራትን በኤጀንሲው ውስጥ ለማከናወን እንዲችል ለማድረግ የራሱ የሆነ መረሃ-ግብር አዘጋጅቷል፡፡

- ፈቃደኛ የሆኑ የኤጀንሲው መ/ቤት ሠራተኞች በየወሩ ከደመወዛቸው የተወሰነ ገንዘብ እያሰባሰቡ ለተስፋ ጐህ ማህበር ገቢ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

- ከተስፋ ጐህ ማህበር ጋር በመተባበር ለመ/ቤቱ ሠራተኞች በኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ላይ የሚያተኩር ድራማ እንዲያዩ ተደርጓል፡፡

- ለ3ኛው ዙር አገር አቀፍ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በተዘጋጁ ፖስተሮች ላይ ስለኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ግንዛቤ የሚሰጡ ጽሑፎች እንዲወጡ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

- ኤጀንሲው ሁለት ኤች.አይ.ቪ /ኤድስን የተመለከቱ ጥናቶችን ከሌሎች መ/ቤቶች በተገኘ የበጀትና የቴክኒክ ድጋፍ አካሂዷል፡፡

18 ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎች

- በክልሎቹ የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ከተከናወነ በኋላ በየወቅቱ አዳዲስ የአስተዳደር ዕርከኖች በመዋቀራቸው ምክንያት በወረዳዎችና በቀበሌዎች ተከናውኖ የነበረው የቆጠራ ካርታ እንደገና እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ ለዚህም ተጨማሪ ወጪ፣ ጊዜና የሰው ኃይል ጠይቋል፡፡ ቢሆንም ከጥቅምት ወር 1999 ጀምሮ ይህ የማስተካከልና አዳዲስ የቆጠራ ቦታ ካርታ የመሥራት ሂደት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

- ለኤጀንሲው በጊዜያዊነት (ለሁለት ዓመት ተኩል) የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቢሮ ተሰጥቶታል፡፡ ቢሮው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ሥራን በተረጋጋ ሁኔታ ለመሥራትና ለመምራት ይረዳል፡፡ ሆኖም ዘላቂ መፍትሄው ኤጀንሲው የራሱ የሆነና በቂ ቢሮ ያለው ሕንፃ ሲገነባ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ከሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር የሚገነባውን የቢሮ ዲዛይን እያዘጋጀ ሲሆን፤ በተጨማሪም ለግንባታ የሚሆን ቦታ ለአዲስ አበባ ባለአደራ አስተዳደር ጠይቆ ምላሽ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ሁሉም አካላት ለሚጠይቁት ትብብር አፋጣኝ መልስ እንዲሰጡ ከወዲሁ እንጠይቃለን፡፡